ታህሳስ 7 ቀን 2003 ዓ.ም

**ሚስተር ኪኒቺ ኦሃሺ**
**በኢትዮጵያ የዓለም ባንክ ተወካይ**
**የ.መ.ሣ.ቁ. 5515**
**አዲስ አበባ**

(በልማት አጋሮች ቡድን ስም)

**ጉዳዩ፡- የልማት እርዳታ እና ሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ**

ውድ ሚስተር ኦሃሺ፡

ይህንን ደብዳቤ የምጽፍልዎ በቅርቡ ሂዩማን ራይትስ ዎች “ልማት ያለ ነፃነት እርዳታ ኢትዮጵያ ውስጥ አፈናን እንዴት እንደሚደግፍ” በሚል ርዕስ ያወጣውን ሪፖርት አስመልክቶ የልማት አጋሮች ቡድን (ዳግ) ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም ላወጣው መግለጫ ምላሽ ለመስጠት ነው።

ሪፖርታችን የኢትዮጵያ መንግስት በለጋሾች የሚደገፉ የልማት ፕሮግራሞችን ለታለመላቸው ዓላማ ከማዋል ይልቅ አፈናን ለማጠናከር እየተጠቀመባቸው መሆኑን በማሳየት በቀረቡት አሳሳቢ ችግሮች ላይ የኢትዮጵያ ለጋሽ ሀገራት ተአማኒነት ያለው ነፃና ዓለማቀፍ የሆነ ምርመራና ማጣራት እንዲደረግ ግፊት እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ነው።

እስካሁን ድረስ በሪፖርቱ የቀረቡትን ክሶች አስመልክቶ ዳግ ምንም ዓይነት ምርመራና ማጣራት አላደረገም።በእነዚህ አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ተአማኒነት ያለውና ነፃ የሆነ ምርመራና ማጣራት እንዲደረግ እርስዎ ቀዳሚውን ሚና እንዲጫወቱ ሂዩማን ራይትስ ዎች አጥብቆ ይጠይቃል። ኢትዮጵያ ውስጥ ይህንን በመሳሰሉ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለማሰባሰብ ያለውን አስቸጋሪነት ጨምሮ በሌላ ማንኛውም ምክንያት ይህንን ምርመራና ማጣራት ማድረግ የማይቻል ከሆነም ይህንኑ በይፋ እንዲገልጹና በኢትዮጵያ ውስጥ የምታካሂዷቸውን ፕሮግራሞች እንዳስፈላጊነቱ ለማሻሻል የሚያግዙ እርምጃዎችን እንድትወስዱ እንጠይቃለን።

አስፈላጊውን ምርመራና ማጣራት ከማድረግና በፕሮግራሞቻችሁ ላይ ያሉትን ቴክኒካዊ የክትትል ዘዴዎች ከማሻሻል ባሻገር ሂዩማን ራይትስ ዎች በሪፖርቱ ያነሳቸውን ሰፋ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የሚመለከቱ ጉዳዮች አብረው እንዲያጤኗቸው አጥብቀን እንጠይቃለን።

መወሰድ ይገባቸዋል በማለት በሪፖርቱ ከቀረቡት ሌሎች እርምጃዎች መካከል ለጋሾች ሀገር በቀል የተጠያቂነትን ሥርዓት ለማስፈን በማሰብ የተቀረጸውን የዲሞክራሲ ተቋማት ፕሮግራም (ዲፕ) ለመደገፍ ለመንግስት ተቋማት የሚያደርጉትን የገንዘብ ድጋፍ መንግስት አፋኝ የሆነውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕግ እስኪያሻሽልና በሰብአዊ መብቶች አያያዝ ረገድ የሚደረጉ መሻሻሎችን ለመለካት የተቀመጡ መስፈርቶችን በመጪዎቹ ወራት እስኪያሟላ ድረስ እንዲቋረጡ እንዲደረግ እንጠይቃለን።

የልማት እርዳታ አጋሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ሰብአዊ መብቶችንና ተጠያቂነትን አስመልክቶ የሚነሱ ችግሮች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ቁልፍ ሚና አላቸው። ከእነዚህም መካከል ለጋሾች ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑንና አፋጣኝ መሻሻል ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን እንደሚገነዘቡና ይህንንም መሻሻል በተግባር ለማየት ጽኑ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ማሳየት ሊሆን ይችላል።

**በዳግ ጥናት ላይ የተስተዋሉ ችግሮች**
የለጋሹ ማህበረሰብ በዳግ አማካይነት ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም ባወጣው መግለጫም ሆነ “የእርዳታ ሥራ አመራርና አጠቃቀም በኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ በሐምሌ 2002 በሰራው ጥናት ያቀረበው ማብራሪያ በሪፖርታችን ለተነሱት በርካታ አሳሳቢ ጉዳዮች ምላሽ የሰጡ አይደሉም።

የዳግ መግለጫ "የልማት እርዳታ ከታቀደው ዓላማ ውጭ ውሏል በማለት የሚቀርቡ ክሶችን በጣም በትኩረት እንከታተላለን" ካለ በኋላ "በሐምሌ 2002 ዳግ ያደረገው ጥናት እንዲህ ያሉ የተቀነባበሩና በስፋት የሚስተዋሉ ችግሮች ስለመኖራቸው ያገኘው ማስረጃ የለም።"[1] በማለት ይደመድማል።

እርስዎም እንደሚያውቁት በዳግ የተደረገው ጥናት ውሱንና በተመረጡ የፕሮግራም አፈጻጸም መከታተያ ስልቶች ላይ የቀረቡ ሪፖርቶችን በቢሮ ውስጥ በመተንተን የተሰራ ሥራ እንጂ እኛ በሪፖርታችን እንደዘገብነው የልማት እርዳታ ከታቀደለት ዓላማ ውጭ ሥራ ላይ የሚውልባቸውን መንገዶችና አካሄዶች አስመልክቶ የተደረገ ምርመራና ማጣራት አይደለም። ይህ የዳግ ጥናት በጉዳዩ ላይ የተደረገ ትክክለኛ ምርመራ ነው ተብሎም አልቀረበም። እንዲያውም ጥናቱ በመግቢያው ላይ "የጥናቱ ትኩረት በለጋሾች የሚደገፉ ፕሮግራሞች ያሏቸው ሥርዓቶችና መጠበቂያ ስልቶች ላይ ነው፤ ምርመራ አይደለም። የልማት እርዳታ ከታቀደለት ዓላማ ውጭ ሥራ ላይ ውሏል በማለት የሚቀርቡ ክሶችን ለማስተባበል ወይም ለክሶቹ ተቃራኒ ማስረጃ ለማቅረብ የተሰራም አይደለም።" በማለት ይገልጻል። (ፓራግራፍ 18)

ጥናቱ በተጨማሪም የልማት ፕሮግራሞቹ አፈጻጸም መከታተያ ዘዴዎች እንዴት እየሰሩ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ንድፈ ሐሳባዊ  ከሆነ ግምገማ በላይ ወደሆነ መደምደሚያ ለመድረስ የመስክ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻል።

> ለፕሮግራሞቹ የተዘረጉት ሥርዓቶችና የመጠበቂያ ስልቶች እንዴት ሥራ ላይ እየዋሉ እንደሆነ ለመረዳት መረጃዎችን ከመፈተሽ በላይ በመሄድ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ከመስክ ማሰባሰብ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ይህ ጥናት በጉዳዩ ላይ ያሉ ወሳኝ መረጃዎችን በግብአትነት የተጠቀመ ቢሆንም ጥናቱ ከዳሰሳ ያለፈ አይደለም። (ቁ. 22)

**በሥራ ላይ ባሉት የክትትል ስልቶች ላይ ያሉ ሕጸፆች**

ጥቅምት 11 ቀን በዳግ የተሰጠው መግለጫ በዳግ ጥናት ውስጥ የቀረቡትን እውነታዎችና ትንታኔዎች አዛብቶ አቀርቦአል። ጥናት የተደረገባቸው አራቱም ፕሮግራሞች ወደተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ይደርሱ ዘንድ "ለመረጃ ማፍለቅና ስርጭት፣ነፃ ለሆነ የክትትል ሥራና የተሻለ ውጤት ለማምጣት ለሚያስፈልጉ ማበረታቻዎች ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልጋቸው" ደምድሟል። (ገጽ vi) በተጨማሪም ጥናቱ ሁለቱ ፕሮግራሞች ከጥበቃና ከክትትል ሥልቶቻቸው ጋር የተያያዙ የተጠያቂነት ሥርኣቶቻቸውን የሚመለከቱ "ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ችግሮች" ያሉባቸው መሆኑን አሳይቷል። (ገጽ vi)

ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ "መልካም" የሚባል የመጠበቂያና የመከታተያ ስልቶች አሏቸው የተባሉት ሁለት ፕሮግራሞች እንኳን እርዳታ ዓላማውን ስቶ ለፖለቲካ መሳሪያነት ሊውል የሚችልበትን ሁኔታ ለይቶ በማሳየት ረገድ ችግር ያለባቸው መሆኑን አሳይቶአል። ይህም ሂዩማን ራይትስ ዎች በጥናቱ ከደረሰበትና በሪፖርቱ እንደችግር ካስቀመጠው ነጥብ ጋር አንድ ዓይነት ነው። ለምሳሌ ጥናቱ የመሰረታዊ አገልግሎቶች  ጥበቃ ፕሮግራም (ፒቢኤስ) ውስጥ ያሉት "የመጠበቂያ ስልቶች በፕሮግራሙ የሚቀርቡ ሽቀጦችና አገልግሎቶች ወይም የሥራ ቅጥር እድሎች በፖለቲካ ወገንተኝነት መመዘኛነት መሰጠታቸውን ወይም ደግሞ ለፒቢኤስ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሰጠው ገንዘብ የፖለቲካ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት መዋሉን ነቅሰው ለማውጣት የሚችሉ አይደሉም።" ይላል። (ፓራግራፍ 66)

እነዚህ በትክክል በሂዩማን ራይትስ ዎች ጥናት የተደረሰባቸው ችግሮች ናቸው። ስለዚህም የለጋሾች እርዳታ ከታሰበለት ዓላማ ውጭ መዋሉ እንዲቆምና ከዓለማቀፍ የልማት አርዳታ ጋር የተያያዙ ሌሎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ ጥበቃዎች እንዲኖሩ ለማድረግ እንዲቻል በእነዚህ ችግሮች ላይ ተጨማሪ ምርመራና ማጣራት ማካሄድ አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን።

አሁን ሥራ ላይ ያሉ የእርዳታ ፕሮግራሞችን የመከታተያ ስልቶች በሂዩማን ራይትስ ዎች የተዘገቡትን ዓይነት ችግሮች ለይቶ ለማውጣት የሚያስችሉ አይደሉም በማለት የዳግ ጥናት የደረሰበት መደምደሚያ መከታተያ ስልቶቹ ያለባቸውን ውሱንነት አስመልክቶ የለጋሽ ድርጅቶች ሃላፊዎች ለሂዩማን ራይትስ ዎች በግል በተደረጉ ውይይቶች ወቅት የሰጧቸውን አስተያቶች የሚያንጸባርቅ ነው። የእንግሊዝ ዓለማቀፍ ልማት ድርጅት (DFID)፣ የካናዳ ዓለማቀፍ የልማት ድርጅት (CIDA)፣ የዩናይትድ ስቴትስ አለማቀፍ የልማት ድርጅት (USAID)፣ የዓለም ባንክና የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን የረድኤት ባለስልጣናት የእርዳታ ለፖለቲካ ዓላማ መዋል ፕሮግራሞቹን የመከታተያ መስፈርት

---

[1] የልማት አጋሮች ቡድን መግለጫ ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ http://www.dagethiopia.org/

አለመሆኑን ለሂዩማን ራይትስ ዎች አጥኚዎች ተናግረዋል። አንደኛው ባለስልጣን "ሰዎች በፖለቲካ ምክንያት እርዳታ እንዳያገኙ ተደርገው ቢሆን እንኳን የፈጣን ምላሽ ግብረ ሃይሉ ይህንን አግኝቶ ነቅሶ ሊያወጣው የሚችልበት መንገድ ያለ አይመስለኝም።" በማለት ለሂዩማን ራይትስ ዎች ተናግረዋል። እ.ኤ.አ በሰኔ 2010 አይሪን የተባለው የዜና አገልግሎት ድርጅት እርስዎ "በቦታው በመገኘት ስውር ምርመራ ካላደረግህ በስተቀር ችግሩን ለማግኘት የሚቻል አይደለም"[2] በማለት መናገርዎን ጠቅሶ ዘግቧል።

በመጨረሻም የዳግ ጥናት በሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት የተዳሰሱትን እንደ የመንግስት አካላት የአቅም ግንባታ ፕሮግራም እና አጠቃላይ የትምህርተ ጥናት ማሻሻያ ፕሮጀክት ያሉ በለጋሾች የሚደገፉ ፕሮግራሞችን በሙሉ የሚዳስስ አይደለም። በመሆኑም በሪፖርታችን የተዘረዘሩትን ችግሮች አስመልክቶ አንድም አይነት ምርመራ ሳያደርግ በሪፖርቱ የተደረሰባቸውን ግኝቶች እንዳለ ውድቅ በማድረግ ዳግ ያወጣው መግለጫ እጅግ አሳሳቢና ለጉዳዩ የማይበጅ ሆኖ አግኝተነዋል።

**በኢትዮጵያ ነፃ የሆነ መረጃ ለማሰባሰብ ያለው ችግር**

የሐምሌ 2002ቱ የዳግ ጥናት እርዳታ ለፖለቲካ መሳሪያነት መዋሉን አስመልክቶ የሚቀርቡ ክሶችን የማጣራት ሃላፊነት የለጋሾች ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስት ነው፤ ምክንያቱም ለጋሾች ይህንን ብናደርግ "የሥራችን ወሰንና ሃላፊነታችን ከሚፈቅደው በላይ መሄድ ይሆንብናል" በማለት ይገልጻል። (ፓራግራፍ 16) ጥናቱ በማከልም ብዙዎቹ የመከታተያ ስልቶች የሚተማመኑት የኢትዮጵያን መንግስት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ አቅም፣ መረጃ እና በትብብር የሚሰሩ ሥራዎችን ነው።

"ቅሬታቸውን ማቅረብ የሚፈልጉ ሰዎች እስርና ሌላም ቅጣት ይደርስብናል ብለው ሊፈሩ ይችላሉ" (ፓራግራፍ 27) በማለት ሲገልጽ የዳግ ጥናት በተዘዋዋሪም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ሀሳብን በነፃ የመግለጽ ነጻነት ላይ ያለውን እጅግ ከባድ አፈና አመላክቷል።

ይሁንና የጥቅምት 21ዱ የዳግ መግለጫም ሆነ የሐምሌ 2002 ጥናቱ የኢትዮጵያ መንግስት የመናገር፣የመደራጀትና የመሰብሰብ ነፃነቶችን ለመደፍጠጥ በሚያራምደው ሰፊ አፈናና በሚያወጣቸው አፋኝ ሕጎች ሳቢያ እየተንሰራፋ በመጣው የፍርሀት ድባብ ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ነጻ ምርመራ ማካሄድ እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን ለመቀበል ለጋሾች ሁለት ልብ የሆኑበትን ዋነኛ ችግር ሳይዳስሱ አልፈዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወት፣ደህንነትና ሥራ ላይ ከሚጋርጠው ዋነኛ ችግር ባሻገር የሰብአዊ መብቶች አጠቃላይ ከባቢ፣ የመንግስቱ ባሕርይ እና ተጠያቂነት ለጋሾች ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ እርዳታ ለማቅረብ የሚኖራቸውን አቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚነካ ነው።

የመንግስትን አሰራርና ተጠያቂነት የሚመለከቱ ጠቃሚ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችሉ የነበሩ በሰብአዊ እርዳታ፣በልማትና በሰብአዊ መብቶች ሥራ ላይ የተሰማሩ ወገኖች እንዲሁም ጋዜጠኞች በመንግስት በሚፈጸምባቸው የተጠናከረ አፈና፣ማሳደድና ክስ ምክንያት ድምጻቸው ታፍኗል።

እርዳታ ኢትዮጵያ ውስጥ ከታቀደለት ዓላማ ውጭ ውሏል በማለት ያነሳናቸው አንዳንዶቹ ችግሮች የእርዳታ ፕሮግራሞቹን አፈጻጸም ለመከታተል ሥራ ላይ በሚውሉት ሥርዓቶች ላይ ቴክኒካዊ ማሻሻያዎችን በማድረግ ሊስተካከሉ የሚችሉ ናቸው። ይሁንና ከእነዚህ በተጨማሪ በፖሊሲ አውጪዎች ምላሽ ማግኘት የሚገባቸው ሰፋ ያሉ የፖሊሲና ከቴክኒካዊ ጉዳዮች የዘለሉ የፖሊሲ ችግሮችም አሉ። በግንቦት ወር 2002 ዓ.ም የተካሄደው ምርጫ በግልጽ እንዳሳየው ኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ያምንም የሕግ ተጠያቂነት በስፋት የሚፈጸሙባት አምባገናናዊ ሥርዓት አራማጅ የአንድ ፓርቲ መንግስት ሆናለች። ይህ ማለት ደግሞ ለጋሾች አሳሳቢ ለሆኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እውነተኛ መፍትሔ ለመስጠት መንግስት ፈቃደኝነቱ አለው ብለው ሊተማመኑ አይችሉም ማለት ነው።

በተጨማሪም በ2001 ዓ.ም በወጡት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትና የጸረ ሽብርተኝነት ሕጎች ሳቢያ የተፈጠረው አፋኝ ሁኔታ ለጋሾች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን አስመልክቶ ከነፃ መገናኛ ብዙሃንና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በሚገኙ ሪፖርቶች ላይ መተማመን እንዳይችሉ የሆኑበትን ሁኔታ ፈጥሯል። በመጨረሻም በተደጋጋሚ የሚታየው የመንግስት ባለስልጣናትና ወኪሎች ለሚፈጽሚቸው የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በሕግ ያለመጠየቅ ሁኔታ፣

---

[2] "ኢትዮጵያ፡ መንግሰት እርዳታ ለፖለቲካ መጠቀሚያነት ውሏል የሚለውን ክስ አስተባበለ" ኤይሪን ኒውስ፤ ጁን 7፣ 2010

ጥሰቶች ይፋ ቢሆኑ እንኳን የሚመረመሩበትና ፈጻሚዎቹ ሕግ ፊት የሚቀርቡበት ዕድል የመነመነ መሆኑን ያሳያል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለጋሾች ስልታዊ በሆነ ሁኔታና በመደበኛነት የእርዳታቸው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖችን የሚመለከቱ ሰፋ ያሉ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን ማንሳትና የሚሰጡት እርዳታም ሰብአዊ መብቶች እንዲጣሱ እያገዘ አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

የዓለም ባንክ፣የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ኢትዮጵያ ውስጥ የልማት ፕሮግራሞችን የሚያካሂዱ የለጋሽ መንግስታት የእርዳታ ድርጅቶች ሂዩማን ራይትስ ዎች በሪፖርቱ ላቀረባቸው ክሶች ጠለቅ ያለና ሰፊ ምላሽ እንዲሰጡ ጥሪውን ያቀርባል። ምላሹ ተአማኒነት ያለው እንዲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች መዳሰስ ይኖርበታል፡-

1. ኢትዮጵያ ውስጥ ተአማኒነት ያለው መረጃ ለማሰባሰብ ካለው አስቸጋሪነትና ይህንኑ በማመንም እርዳታ ለፖለቲካ ዓላማ መዋሉን በትክክል ለማረጋገጥ የዓለም ባንክ ዳይሬክተር ስውር ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ከመግለጻቸው አንጻር ለጋሾች የቀረቡትን ክሶች እንዴት ሊመረምሯቸው አስበዋል?
2. የመሠረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ ፕሮግራምን (ፒቢኤስ) አፈጻጸም መከታተያ ስልቶች "በፕሮግራሙ የሚሰጡ ሽቀጦችና አገልግሎቶች ወይም የሥራ ቅጥር ዕድሎች በፖለቲካ ወገንተኝነት መመዘኛነት መሰጠታቸውን ወይም ለፒቢኤስ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሰጠው ገንዘብ የፖለቲካ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት መዋሉን ነቅሰው ማውጣት የሚችሉ አይደሉም" ከመባሉ አንጻር እንዲህ ያለውን ችግር ለመከታተል ለጋሾች በመከታተያ ስልቶቹ ላይ ሊያደርጉ ያሰቡት ለውጥ ምን ዓይነት ነው?
3. ለጋሾች እርዳታ ከታሰበው ዓላማ ውጭ በኢትዮጵያ መንግስት ሥራ ላይ እየዋለ አለመሆኑን በየሀገሮቻቸው ላሉ ግብር ከፋዮች ለማረጋገጥ ያለባቸውን ሃላፊነትና የኢትዮጵያ መንግስት እርዳታን ለፖለቲካ መጠቀሚያ አውሎታል በማለት የሚቀርቡ ክሶችን የመመርመር ቀዳሚ ሃላፊነት የራሱ የኢትዮጵያ መንግስት ነው የሚለውን አባባላቸውን እንዴት ያስታርቃሉ?
4. የመሰረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ ፕሮግራም (ፒቢኤስ) አካል የሆነውን ማህበራዊ ተጠያቂነትን የሚመለከተውን ክፍል ተፈጻሚነት መከታተልን ጨምሮ ኢትዮጵያውያን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በርካታ የሰብአዊ መብቶችና የአድቮኬሲ ሥራዎችን እንዳይሰሩ ያደረገው የበጎ አድራጎት ደርጅቶችና ማህበራት ሕግ የፈጠረውን ተጽዕኖ ለጋሾች እንዴት መፍትሔ ሊሰጡት አስበዋል?

መልስዎን እጠብቃለሁ

አክባሪዎ

ኬኔት ሮዝ
ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-

በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የኔዘርላንድስ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የዴንማርክ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የኖርዌይ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የካናዳ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የአየርላንድ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የስዊድን ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የፊንላንድ ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የስፔን ኤምባሲ
በኢትዮጵያ የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ልዑክ
በኢትዮጵያ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ

የኢጣሊያ የወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
የጀርመን የልማትና ተራድኦ ድርጅት/ጂቲዜድ/
የኔዘርላንድስ የልማት ድርጅት/ኤስኤንቪ/
የአውሮፓ ኮሚሽን
የስፔን አለማቀፍ የልማት ድርጅት/ኤኢሲአይዲ/
የስዊድን ዓለማቀፍ የልማት ትብብር ድርጅት /ሲዳ/
የካናዳ ዓለማቀፍ የልማት ድርጅት/ሲዳ/
የኖርዌይ የልማት ትብብር ድርጅት/ኖራድ/
የዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ዳኒዳ/
የአየርላንድ እርዳታ ድርጅት
የዩናይትድ ስቴትስ አለማቀፍ የልማት ድርጅት/ዩኤስኤይድ/
የፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
የእንግሊዝ ዓለማቀፍ የልማት ድርጅት/ዲኤፍአይዲ/
የፈረንሳይ የልማት ድርጅት/ኤኤፍዲ/
ሚስስ ኦቢጌሊ ካትሪን ኢዚክዊሲሊ፡ በኣለም ባንክ የአፍሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት